# በፌዴራል ጤና ሚኒስቴር
# የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
# ዜና ኢ.ሕጤ.ኢ.

መስከረም 2014 ቅጽ 5 ቁጥር 5

በኢ.ሕጤ.ኢ. የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ቢሮ በየወሩ የሚዘጋጅ


## የህጻናት ሞት መንስኤ ዙርያ ጥናቶች ተከናወኑ



የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የብሔራዊ የጤና መረጃ አስተዳደር ቅመራና ትንተና ማዕከል በሀሮማያ ዮኒቨርስቲ ከሚካሄደው ከቻምፕስ ፕሮጀክት ጋር በመቀናጀት የህጻናት ሞት መንስኤ እና ደረጃ ጠቋሚ የሆኑ የጥናት ውጤቶችን ለባለደርሻ አካላት ያደረሰበትን ስብሰባ በዛሬው እለት በኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ አከናወነ፡፡ ዶ/ር አለምነሽ ኃይለማርያም በኢንስቲትዩቱ የብሔራዊ የጤና መረጃ አስተዳደር ቅመራና ትንተና ማዕከል ከፍተኛ ተመራማሪና አስተባባሪ በስብሰባው መክፈቻ ላይ እንዳስገነዘቡት ማዕከሉ ለጤና ሥራዎች ግብአትና ለፓሊሲ ትግበራ እንዴት ጥቅም ላይ መዋል እንደሚቻል በዝርዝር ያስረዱ ሲሆን የባለድርሻ አካላት ተሳትፎም እጅግ ወሳኝ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ስብሰባው የህጻናት ሞት መንስኤ እና ደረጃ ጠቋሚ የሆኑ የጥናት ውጤቶችን ለባለድርሻ አካላት ከማድረስ በተጨማሪ የጥናት ውጤቶችን ለፖሊሲ ፕሮግራም ግብአትነት ሊውሉ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ እንደሚመክር የታወቀ ሲሆን አገር አቀፍ የሆኑ የጥናት ውጤቶችን አጠቃቀም ላይ የባለድርሻ አካላትን ልምድ ለማዳበርና ምክረ ሀሳቦችን ለማመንጨት ብሎም ዘመኑን የዋጀ የዳታ ቅመራና ዘዴዎችን በመጠቀም የፕሮጀክቱን የጥናት ውጤቶች ማቅረብ ላይ እንደሚያተኩር ለማወቅ ተችሏል፡፡ በስብሰባው ላይ ልዩ ልዩ ጥናታዊ ግኝቶች ቀርበው ውይይቶች ተካሂደባቸዋል፡፡

## ሀገር አቀፉ የብሔራዊ የጤና ደህንነት መርሀ ግብር አፈጻጸም ስብሰባ ተከናወነ



በተቀናጀ እና በተናበበ መልኩ የሚከናወን ብሄራዊ የጤና ደህንነት መርሀ-ግብር ስኬታማ መሆን ለአጠቃላይ ሁለንተናዊ ለሆነው ሀገራዊ የጤና ድህንነት ስርአታችን አቅም መጎልበት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው ተገለጸ፡፡

አቶ አስቻለው አባይነህ የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ም/ዋና ዋና ዳይሬክተር በአዳማ ከተማ በተከናወነው የኢትዮጵያ ብሔራዊ የጤና ደህንነት መርሀ ግብር አፈጻጸም የምክክር ስብሰባ ላይ በመገኘት ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር ላይ እንዳስገነዘቡት ምንም እንኳን የሀገሪቱ የጤና ስጋቶችን የመከላከል፣ ሲከሰቱም ፈጥኖ የመለየትና አፋጣኝ ምላሽ የመስጠት አቅምን ለማጎልበት የሚረዱ ልዩ ልዩ መሠረታዊ የማስቻያ ሁኔታዎችን የተከናወኑ እና እየተከናወኑ ቢሆንም አሁንም ቢሆን የጤና ስርዓቱን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ የሚረዱ ነገር ግን ያልተከናወኑ ቀሪ ተግባራት እና ሀገራዊ ፕሮግራሞችን በመፈጸምና በማስፈጸም ረገድ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ትብብር እንዲሁም ንቁ ተሳትፎና ርብርብን

. . .ወደ ገጽ 2 ዞሯል

## . . . ሀገር አቀፉ የብሔራዊ

. . .ከገጽ 1 የዞረ

አስፈላጊ በመሆኑ ሁሉም ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ድርሻ እንዲወጡ አሳስበዋል።

ምክትል ዳይሬክተሩ አያይዘውም የብሄራዊ ጤና ደህንነት መርሀ-ግብር ስኬታማ መሆን ለአጠቃላይ ሁለንተናዊ የጤና ድህንነት ስርአታችን አቅም መጎልበት ከፍተኛ እና በሁሉም የአስተዳደር እርከኖች ያሉ የጤና ስርአት መሻሻልና ለጤና ስጋቶች ያለንን ዝግጁነት፣ የመከላከል፣ የመለየትና ፈጥኖ ምላሽ የመስጠት ሁለንተናዊ አቅማችንን ለማጎልበት ከማስቻሉም በላይ ከራሳችን አልፎ ሀገራችን የፈረመችበትን የዓለም ጤና ዋስትና መረጋገጥ ጉልህ አስተዋጽኦ ለማበርከትና ብሄራዊ ግዴታችንን ለመወጣት ያስችለናል ብለዋል።



በምክክር መድረኩ ላይ ከልዩ ልዩ የመንግስት እና አጋር ተቋማት የተወከሉ ባለሙያዎች በስብሰባው መድረክ ላይ መገኘታቸውን ለማወቅ ተችሏል።

# የብሂራዊ የጤና መረጃ አስተዳደር፤ ቅመራና ትንተና ማዕከልን እያከናወናቸው የሚገኙትን ተግባራት አስመልክቶ ከማዕከሉ ሃላፊዎች ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ

## . . . ከባለፈው እትም የቀጠለ





ጥያቄ- በአገራችን በተለይ ከጤናና ጤና ነክ ዳታዎች ጋር በተያያዘ ከዳታ አያያዝና አስተዳደር ጋር የሚነሱ ዋና ዋና ችግሮች ምን ነበሩ?

ዶ/ር ዓለምነሽ - ይታዩ የነበሩ ችግሮችን በሶስት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን፡ :የመጀመሪያው የሚሰሩ ምርምሮችና ዳታዎች በተመለከተ የመረጃ ልውውጥ ልምድ አለመኖሩ ተጠቃሽ ነው፡ :ለምሳሌ አንድ ጥናት ከተሰራ በሁዋላ የዳታ ባለቤትነት ጉዳይ ሲነሳ የሚሰሩ ጥናቶች የኢንስቲትዩቱ ሳይሆን የተመራማሪው የራሱ የግሉ ንብረት አድርጎ የማየት ልምድ ነበር።ስለሆነም ይህን የባለቤትነት እሳቤ ለማስተካከል የዳታ ማጋሪያ መመሪያዎችን በማሻሻልና በማዘጋጀት ዳታዎችን ወደአንድ ቋት ለማከማቸት በቅድሚያ አዲስ አስተሳሰብና አዲስ ባህል ማስተዋወቅ ያስፈልጋልና ይህን ለማምጣት ብዙ ርቀት ሄደናል።እንደ ኢንስቲትዩት ደግሞ ዳታዎችን ከሌላ ተቋም ስናመጣ የምንረከብበት አሰራር አልነበረንም፤ በመሆኑም ይህን ክፍተት የሚያስተካክል የመግባቢያ ሰነድ አዘጋጅተናል፡ :መመሪያም እየተዘጋጀ ነው።

ሌላው ችግር ዳታዎች የሚቀመጡበት የዳታ መሰረተ-ልማት(መዋቅር)አልነበረም። ይሄ ትልቅ ፈተናም ነበር። የኢንተርኔት አቅሙ፤መሰረተ-ልማቱ፤ለስራው አጋዥ የሆኑት ቁሶች፤የሶፍትዌርና ሃርድዌር አቅሙ በአጠቃላይ ኢንስቲትዩቱ ይህን ትልቅ ስራ የሚያስተዳድርበት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አቅምና ብቃቱ መፈተሽ ነበረበት።ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር የአይቲ ኦዲት ሰርተውልናል፤ ይህ ቴክኖሎጂ ነክ ዳሰሳ ከተጠና በሁዋላ ለዚህ ስራ አስፈላጊ የሆነ የቴክኖሎጂ መሰረተ-

# የብሄራዊ የጤና መረጃ አስተዳደር፤...ቃለ መጠይቅ

ልማት የማስተካከል ስራ ፈታኝ ቢሆንም ተሰርቷል፤የመሳሪያ ግዥና ተያያዥ ስራዎችም ተሰርተዋል።በዚህ መስረት ከፍተኛ አቅም ያለው ሰርቨር እና የዳታ ሴኩውሪቲውን ለማጠናከር አስተማማኝ ደህንነት መፍጠር፤ዳታ ሴኩሪቲን የሚያግዝ ገዥ መመሪያ የማዘጋጀት እና በቀላሉ በኔትወርክ ዳታ የሚገኝበትን አሰራር በመዘርጋት ሂደት ላይ እንገኛለን።ወደ 8 ሚሊዮን ብር ገደማ የሚያወጣ የዳታ መሰረተ- ልማት ለመገንባት የሚያስችል ዝግጅት እያደረግንም እንገኛለን።

ዶ/ር አወቀ- እንግዲህ ከላይ እንደተገለፀው አዲስ የዳታ ስርዓት መፍጠር በጣም ከባድ ጥረት ይጠይቃል። ተመራማሪዎች ኢንስቲትዩቱን ለቀው ሲሄዱ የሰሩትን የምርምር ስራ ዳታ ሳያስረክቡ የመሄድ ልምድ ነበር እናም ዳታዎችን ለመረከብ በጣም ከባድ ፈተና ነበረብን። የዳታ ሳይንስን ተረድቶና ለሌሎችም ግንዛቤውን ፈጥሮ የአይቲ መሰረተ-ልማቱን ማቀድና ማዘጋጀትም ትልቅ ስራ ይጠይቃል።በርካታ ስራዎች ይጠይቃል። በርካታ ወይይቶች፣ ስምምነቶች፣ አሰራሮች፣ ስትራቴጂክ ፕላኖች፣ የመግባቢያ ሰነዶች፣ የተለያዩ መመሪያዎችን እና መፈተሽ እና ማዘጋጀት ይጠይቅ ነበር፣ ፈተናም ያየንበት ነበር። እንደግለሰብም እንደቡድንም ስለለውጥ የተማርንበት አጋጣሚ ነው ለማለት እችላለሁ።በዚህ አጋጣሚ ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈሉትን ዶ/ር ኤባን ጨምሮ ዶ/ር ዓለምነሽን፤የየክፍሉን የስራ ሃላፊዎች፤ዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲን ለማመስገን እፈልጋለሁ።

የሰው ሃይል ማሟላቱም ሌላው ፈተና ነበር፤የስራውን ባህሪና ፍላጎት የተረዳ ባለሙያ በመፈለግ ቀጥረናል፤በአሁኑ ወቅት 36 ባለሙያዎች በማዕከሉ ውስጥ ይገኛሉ። እነዚህን ሁሉ በማስተካከል ማዕከሉ ስራ ጀምሯል።

ጥያቄ- ማዕከሉ ስራ ከጀመረ በሁዋላ በአራት ንዑስ ክፍሎች ተደራጅቶ ስራ ጀምሯል፤ እስኪ ስለእነዚህ ክፍሎች ዓላማና ተግባር አብራሩልን?

ልክ ነው፤ማዕከሉ በአራት ኬዝ ቲሞች ተዋቅሯል።በዝርዝር እንመለከታቸዋለን።

1. የጤና የዳታ ክምችትና አስተዳደር ቡድን (Health Data Repository and Governance case team)

የዚህ ኬዝቲም ዓላማ የጤና ዳታዎችና መረጃዎች ከተለያዩ ምንጮች በማሰባሰብ፤ደረጃውን የጠበቀ የመረጃ ቋት ማዘጋጀት፤ማደራጀትና የመረጃ ጥራትን ማረጋገጥ ነው። በተጨማሪም አገራዊና አህጉራዊ እንዲሁም አለምአቀፋዊ ዲጂታል የጤና ዳታ ስርዓት በመዘርጋትና መስተጋብር በመፍጠር የዳታ ልውውጥን ማሳለጥ እንዲሁም የዳታ ማጋራት እና የመጠቀም ባህልን ማሳደግ ነው።

2. የጤና ዳታ ቅመራ ሞዴሊንግ እና ቪዥዋላይዜሽን ኬዝ ቲም (Health Data Analytics, Modeling and Visualization case team)

የዚህ ኬዝቲም ዓላማ የላቀና ዘመኑን የዋጀ ቴክኖሎጂዎችን ለምሳሌ ያህል እንደ ሰዉ ስራሽ ብልሀት (Artificial intelligence, machine learning, data mining) በመጠቀም የጤና ዳታ ቅመራን ከፍተኛ ደረጃ ማድረስ ዓላማ ያደረገ ነው። የሞዴሊንግ ትንበያ፤ የረቀቁ የስታትስቲክስና የሂሳብ ቀመሮችን እንዲሁም ዳታ ሳይንስ (Data Science) በመጠቀም ለጤናው ዘርፍና ለህብረተሰብ ጤና ገላጭ የሆኑ ቀመሮችን ሰዎች በቀላሉ በሚረዱትና በቀላሉ የሚያገኙበትን ስርዓት በመዘርጋት ተደራሽ ማድረግ

3. የጤና ማስረጃ ትንተናና ስርጸት ቡድን (Health Evidence Synthesis& Translation case team)

ይህ ኬዝ ቲም ሁለት ዓላማዎች አሉት፤

1.የጤናና ጤና ነክ ፖሊሲዎችን ስትራቴጂዎችን ፕሮግራሞችን ትግበራና ውጤታማነት መረጃና ማስረጃዎችን በማጠናቀር ክትትል፤ ግምገማ፣ እንዲሁም ትንተና በማድረግ ለጤናው ዘርፍና ለህብረተሰብ ጤና አስፈላጊውን የማስረጃ ግብዓት መስጠት

4. 2.በማዕከሉ የተተነተኑ ማስረጃዎች ጥቅም ላይ ይውሉ ዘንድ የተለያዩ ስርዓቶችን በመዘርጋት ለፖሊሲ አውጪና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግና የመረጃ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ የበሽታዎች ጫናና ስርጭት (Burden of Diseases case team)

የዚህ ኬዝቲም ዓላማ በአገርአቀፍ፤በክልልናበወረዳ ደረጃ የበሽታዎችንና አጋላጭ መንስኤዎቻቸው የሚያደርሱትን ጫናና ስርጭት ህልፈተ ህይወት እንዲሁም ያለዕድሜ መቀጨት በጊዜ፣በፆታ ፣በዕድሜ ሳይንሳዊ አሰራርን ተከትሎ ጥናቶችን ማካሄድና ልኬቶች ማቅረብ ነው።

ጥ- እስካሁን ምን ያህል ዳታዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል?

ዶ/ር ዓለምነሽ - እስካሁን ካነጋገርናቸው 60 መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ 40 ያህሉ ዳታ ሰጥተውናል፡ ፡በክልል ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩቶች ውስጥ ያሉ ዳታዎችንም ሰብስበናል።ቀደም ሲል የኢንስቲትዩቱ ባልደረባ የነበሩ ባለሙያዎች ነገር ግን አሁን ተቋሙን ለቀው የሄዱ በርካታ ተመራማሪዎች አሉ፤ከእነሱ ጋር በመፃፃፍ ዳታ እንዲሰጡን አድርገናል።ከሴሮ እና ከፕላን ክፍል ጋር መረጃ በመሰብሰብ ዳታ የሌላቸውን ቴክኒካል ሪፖርት ለማሰባሰብ ጥረት አድርገናል።በኢንስቲትዩቱ ከጥንት ጀምሮ የታተሙ ከ 1700 በላይ የምርምር ህትመቶችንም አከማችተናል።

ለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን!!